# ቅንጅት ቫንኮቨር

## በቅንጅት ለአንድንትና ዲሞክራሲ ፓርቲ ሊቀመንበር በአቶ ኃይሉ ሻዉል ታህሳስ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ያወጡት መግለጫ አሳሳቢ በመሆኑ በቫንኮቨር ቅንጅት ድጋፍ አካል የተወሰደ አቋም

### መግቢያ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለፍትህ የቆመ መሪ ባለማግኘቱ መራራ የአስተዳደር በደል ከገጠመው ዘመናት አስቆጥሮል። የአፄዉ ሹማምንት፣ የደርግ መለዮ ለባሾችን ጨምሮ እስከ የጫካዉ ጎፈሬ ወያኔ ድረስ ያሉት የአገዛዝ አይነቶች ባመዛኙ በኋላ ቀርነት፣ በግትርነት፣ በስልጣን ዋልጌነት፣ በግድያና በማስፈራራት እንዲሁም በከፋፈለህ ግዛው ላይ የተመሰረቱ ናቸዉ። የኢትዮጵያ ሕዝብም እነዚህን አገዛዞች ተቃዉሞ ትግሉን ቀጥት ይገኛል። በመሆኑም የቫንኮቨር ቅንጅት ድጋፍ የወቅቱን ሁናቴ በሚመለከት የሚከተለዉን ጥሪ አቅርበናል።

### ለኢትዮጵያ ሕዝብ !

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ ልንገልጽ የምንፈልገው የተግሉ ዋናዉ ባለቤት እናንተዉ በመሆናችሁ ችግሩን የሚያባብሱትን፣ ለከፋ አገዛዝ አሳልፈዉ የሚሰጧችሁን እንደዚሁም ፀረ- ዴሞክራሳዊ ኃይሎችን ማንነት በሚገባ ለይታችሁ ስለምታዉቁ በብሄረሰብ፣ በቋንቋ በሀይማኖትና በትዉልድ ቀዬ ሊከፋፍሏችሁ አደባባይ ከተነሱት ጠላቶች ጎን ተመሳሳይ ዓላማ የሚያራምዱትን ከእኛ ይበልጥ እናንተ ታዉቋቸዋላችሁ በመሆኑም ትግሉን አጠናክራችሁ እንድትቀጥሉ እያሳሰብን እኛም የበኩላችንን ድጋፍ በገንዘብ በዲፕሎማሲ እና በመሳሰሉት ሁሉ አጠናክረን እንደምንቀጥል እናረጋግጣለን።

### ለቅንጅት ፓርታ አባለት በሙሉ!
### ለቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ምእራፎች በሙሉ!

የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የተመሰረተበት አላማ ለፍትህ የበላይነት ፣ለዲሞክራሲ አሰራር መስፈን፣ለሰብአዊ መብት

መከበርና እንደዚሁም የግለሰብ ነፃነትን የሚጠብቅ ስርአት በኢትዮጵያ ዉስጥ ለማስፈን ነዉ። ይህ መርህ ሲጣስ አባለትም ሆኑ ደጋፊዎች ሆ ብለን በተቃውሞ በመነሳት በ10ሺህ የሚቆጠሩ የታሰሩለትን በርካታዎች የሞቱለትን ሌሎች ደግሞ ቤት ንብረታቸዉን ጥለዉ የተሰደዱበትን ትግል ማጠናከርና ለግብ የማብቃት ተልእኮአችንን ለመወጣት ይበልጥ በህብረት እንድንነሳ ጥሪ እናደርጋለን፤

## ለወያኔ /ኢሕአዴግ አባላት

ለወያኔ /ኢሕአዴግ አባላት የምናስተላልፈዉ መልእክት ቢኖር በአሁኑ ወቅት በቅንጅት ዙሪያ የተፈጠረዉ ችግር ፓርታዉን ይበልጥ ያጠራዋል እንጂ በእናንተ ተንኮልና ሴራ እንደማይቲከም እያረጋገጥን፤ በሕዝብ የተመረጡ የፓርቲዉ አባላት ሀላፊነታቸዉን እንዳይወጡ የምታደርጉትን ደባ እንድታቆሙ እናስገነዝባለን!

## ለአቶ ኃይሉ ሻውል

ቅንጅት በ1997 ዓ. ም ምርጫ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይሁንታ አግኝቶ መመረጡ የሚታወቅ ነዉ። በዚህ ሂደት እርሰወም የፓርቲዉ መሪ ሁነዉ በወያኔ እኩይ ተግባር መንግስት ባይመሰርቱም በኢትዮጵያ ሕዝብ ልቦና መንግስት ሆነዉ እዉቅና አግኝተዋል። ሁኖም የተሰጠዎትን ታሪካዊ ሀላፊነት በአግባቡ ከመወጣት ይልቅ የፓርቲዉን ዴሞክራሲያዊ መርህ በመጣስ ያደረጉት እንቅስቃሴ በጣም አሳዝኖናል በመሆኑም የቫንኮቨር ቅንጅት ድጋፍ ሰጭ አባላት የሚከተሉትን ባስቸኳይ ተግባራዊ እንዲሆኑ በአክብሮት እንጠይቃለን።

1. በስቸካይ ወደ አገር ቤት ተመልሰዉ የቅንጅት ላእላይ ምክር ቤቱን በመሰብሰብ ለፓርቲዉ ወቅታዊ ችግሮች አንገብጋቢ መፍትሄ እንዲያፈላልጉ፤
2. ታህሳስ አንድ ቀን 2000 ዓ.ም የፃፉትን 5ቱን የሥራ አስፈፃሚ አባላት የሚያግደዉ ዉሳኔ ከስልጣንወ በላይ መሆኑን እንዲገነዘቡ እናሳስባለን፤
3. በግል የመሰረቱትንና በኋላም ከሌላዉ ወገን ጋር ያፈረሱትን የቅንጅት አለማቀፍ ምክር ቤት እንደገና እየተጠቀሙበት በመሆኑ ይህ ድርጅት ለቅንጅት ህልውና ተፃራሪ በመሆኑ በአስቸካይ መፍረሱን በድጋሚ እንዲያረጋግጡ።

ከላይ የተዘረዘሩትን እርምጃዎች በአስቸካይ ሳይወስዱ ቢቀሩ የቫንካቨር ቅንጅት ምእራፍ የሚቀጥሉትን እርምጃዎች ይወስዳል።

1. ቫንኮቨር ቅንጅት ምእራፍ ለእርሰዎ የሚሰጠዉን የመሪነት ድጋፍ ያነሳል።
2. የቫንኮቨር ቅንጅት የሚከተለዉ የብዝሃን አመራር (COLLECTIVE LEADERSHIP) ይሆናል።
3. በእርሰዎ በኩል ማንኛዉም የገንዝብም ሆነ የማቴሪያል ድጋፍ መስጠት ያቆማል።
4. በዚህ አፍራሽና ከፋፋይ ትግባርዎት የሚቀጥሉ ከሆነ ቫንኮቨር ቅንጅት ባገኘዉ አጋጣሚ ሁሉ ተቃዉሞውን እንደሚገልፅ እናስታዉቃለን።

ሕዝባችን ለፍትህ ለዲሞክራሲና ለእኩልነት በሚያደርገው ትግል ከጎኑ መቆማችንን በዚህ አጋጣሚ እንረጋግጣለን።

ቅንጅት ቫንኮቨር